አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፷፭
አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፭

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st year No. 65
Addis Ababa፣ August 25th , 2023


**ማውጫ**


ደንብ ቁጥር ፻፶፭/፪ሺ፲፭
የመኖሪያ ቤት ኪራይ ጭማሪን ለ፺ ቀናት ለማገድ የወጣ ማሻሻያ ደንብ
ገጽ------------------------------ ፫ሺ፲፮


**CONTENTS**


Regulation Number 155/2023
A Regulation to Provide for the Amendment for the Suspension of Residential Housing Rental Increment for 90 days
Page--------------------------------------------- 3016


## ደንብ ቁጥር ፻፶፭/፪ሺ፲፭

## የመኖሪያ ቤት ኪራይ ጭማሪን ለ፺ ቀናት ለማገድ የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፳፪/፪ሺ፲፫ እንደገና ለማሻሻል የወጣ ደንብ

በከተማው አስተዳደር ከግለሰብ የመኖሪያ ቤት ተከራይ የሆኑ ነዋሪዎች ላይ በአከራዮቻቸው ሚዛናዊ ከሆነው የቤት ኪራይ ዋጋ በላይ ጭማሪ እየተደረገ በመሆኑ አብዛኛው የከተማው ነዋሪ ተከራይ ለምሬት ከመዳረጉም ባሻገር የዋጋ ጭማሪው፣ ከአቅም በላይ የሆነ ኪራይ ማስከፈል፣ ተከራዮች ያለአግባብ በአከራዮቻቸው ፍላጎት ከተከራዩበት መኖሪያ ቤት እንዲወጡ ማድረግ፣ በአከራይ ተከራይ ግንኙነት አለመግባባት መፍጠሩ እና ለእንግልት መዳረጋቸው አሁንም የህዝብ እሮሮ እየቀረበበት በመሆኑ ችግሩ እስኪቃለል ድረስ በጊዜያዊነት የመኖሪያ ቤት ኪራይ ጭማሪን ማገድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤


ያንዱ ዋጋ……….
Unit price……….


## Regulation Number 155/2023

## A Regulation to Provide for the Re-Amendment of regulation No. 122/2013 issued for the Suspension of Residential Housing Rental Increment for 90 days

**WHEREAS,** the housing rental price has been increasing unfairly by landlords beyond the reasonable rental price on tenants, the request of unfair rental price, the inappropriate eviction of tenants based on the interest of the landlord, and the existence of conflict between tenants and landlords have created exasperation on the residents of the city and such has caused sufferings and intense dissatisfaction of the public; and therefore, it has been found necessary to temporarily suspend the residential housing rental increment until addressing the problem;


አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፸፬/፪ሺ፲፬ አንቀፅ ፺፪ መሰረት ይህን ማሻሻያ ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የመኖሪያ ቤት ኪራይ ጭማሪን ለ፺ ቀናት ለማገድ የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፳፪/፪ሺ፲፫ እንደገና ለማሻሻል የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፶፭/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ማሻሻያ</u>

የመኖሪያ ቤት ኪራይ ጭማሪን ለ፺ ቀናት ለማገድ የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፳፪/፪ሺ፲፫ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩ የደንቡ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ተተክቷል፡-

"፬. <u>ስለዕገዳ</u>

፩ በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበ ሆኖ ከነሐሴ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም እስከ የካቲት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም መኖሪያ ቤት ማስለቀቅ እና በመኖሪያ ቤት ላይ የሚደረግ የኪራይ ዋጋ ጭማሪ የተከለከለ ነው፡፡"

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 92 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 74/2021, the Cabinet of the Addis Ababa City government has issued this amendment Regulation.

1. **<u>Short Title</u>**

   This Regulation may be cited as: "Re-Amendment for Regulation No. 122/2021 issued for Suspension of Residential Housing Rental Increment for 90 days Regulation No. 155/2023."

2. **<u>Amendment</u>**

   Regulation No. 122/2021 that was issued for the suspension of residential housing rental increment for 90 days is hereby amended as follows.

   1. Sub-Article (1) of Article 4 of the Regulation is cancelled and replaced by the following Sub-Article:

   "**4. <u>About Suspension</u>**

   1. Without prejudice to the provisions of other laws, eviction from the house and a rental increment on residential houses from August 25th, 2023 to February 21th, 2024 is prohibited."

፫. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከነሐሴ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም ጀምሮ የጸና የሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

3. <u>**Effective Date**</u>

This Regulation shall enter into force as of this August 25th, 2023.

**Done at Addis Ababa, this August 25th, 2023**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**